# የ1997 በጀት የምግብ ዋስትና ፕሮግራም የፊዚካል ሥራዎች ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

## ክፍል አንድ፡- የሰፈራ ፕሮግራም

### 1.1. ትግራይ ክልል

- *15000 የቤተሰብ ኃላፊዎችን ለማስፈር ታቅዶ 12984 እንዲሰፍሩ ተደርጓል፡፡*
- *ለበሬና ዘር መግዣ የታቀደው ብር 10,550,000 ሲሆን 12,549,225 ብር በብድር መልክ ተሰጥቷል፡፡ ለ12,984 ቤተሰቦች /የተገዛውን በሬና ዘር መጠን አይጠቅስም/*

*መሠረተ ልማት*

- *22 የእጅ ጉድጓድ ለመቆፈር ታቅዶ 14 ተቆፍሯል፣*
- *40 ኪ/ሜ መንገድ ለመሥራት ታቅዶ 43 ኪ/ሜ ተሰርቷል፣*
- *አጉበር ለ12,984 ቤተሰብ ታቅዶ ለሁሉም ተሰጥቷል፡*

### 1.2. አማራ ክልል

- *50000 ቤተሰብ ለማስፈር ታቅዶ 31924ቱ እንዲሰፍሩ ተደርጓል፣*
- *የተሰጣቸው መሬት 30,538 ሄ/ር ነው፣*
- *ከ12,428 በላይ የእርሻ በሬ ተሰራጭቷል፡፡ /ዘሩ መጠኑ እለተጠቀሰም/*

*መሠረተ ልማት*

- *506 ኪ/ሜ መንገድ ለመጠገን ታስቦ 403.6 ኪ/ሜ ተጠግኗል፣*
- *526 ኪ.ሜ አዲስ መንገድ ለመሥራት ታስቦ 558.4 ኪ/ሜ ተሰርቷል፣*
- *58 መለስተኛ ጉድጓድ ለመቆፈር ታቅዶ 91 መለስተኛና 4 ጥልቅ ጉድጓድ ተቆፍሯል፣*
- *15 ሣተላይት ጤና ኬላዎችና 5 ጤና ኬላዎች ታቅደው 16 የሳተላይት ጤና ኬላዎችና 3 ጤና ኬላዎች ተገንብቷል፣*
- *16,250 አጉበር ተሰራጭቷል፣*
- *ከታቀደው 29 የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ 25ቱ ተገንብቷል፣*

## 1.3 ኦሮሚያ ክልል

- 30,234 የእርሻ በሬዎችን ለማቅረብ ታቅዶ 7,720 ተገዝቷል፣
- ከታቀደው 60,128 የፍየሎች ግዢ ውስጥ 49,162 ፍየሎች/በጐች ተገዝተዋል፣
- 5,330 ሄ/ር መሬት በትራክተር ለማሳረስ ታቅዶ 9025 ሄ/ር መሬት ታርሷል፣
- ከታቀደው የ102 የገበሬዎች ማሰልጠኛ ማዕከላት ውስጥ 31 ተጠናቀዋል፣ ነገር ግን የ11ዱ ግንባታ ገና ነው።
- 55,000 ሄ/ር መሬት ለማከፋፈል ታቅዶ 98,611 ሄ/ር ተከፋፍሏል፣
- ከታቀደው 10,000 አዲስ ሰፋሪዎች ውስጥ 6,845ቱ ሰፍረዋል፣
- 10,000 ፍየሎች ለመግዛት ታቅዶ 2,978 ፍየሎች ተገዝተዋል፣
- ከዕቅዱ 210,384 ዶሮዎች ውስጥ 12,145 ዶሮዎች ተገዝተዋል፣
- 10,240 የንብ ቀፎ ለመግዛት ታቅዶ 1,900 ተገዝቷል፣
- 14041 ኩንታልየተለያዩ የሰብል ዘሮችን ገዝቶ ለማቅረብ ታቅዶ 22451.8 ኩንታል ተገዝቷል፣
- 82,707 ኩንታል ኬሚካል ማዳበሪያ ለመግዛት ታቅዶ 45,304 ኩንታል ተገዝቷል፣
- 7,386 ምድጃዎች ለመግዛት ታቅዶ ሁሉም ተገዝቷል፣
- የሶላር ኩከር ተከላና የመዘርጋት ሥራ ተከናውኗል፣ /መጠኑና ብሩ አልተጠቀሰም/
- የመስኖ ግንባታና የውኃ ማቆር ሥራ ተሰርቷል፣ /መጠኑና ብሩ አልተጠቀሰም/
- 151,633 ኩንታል የሰብል ምርት ግዢ ታቅዶ 27,493 ኩንታል ተገዝቷል፣

### መሠረተ ልማት

- ከታቀደው 126 የውኃ ጉድጓድ ውስጥ 113ቱ ተቆፍሯል፣
- 720 ኪ.ሜ መንገድ ለማደስ ታቅዶ 463.25 ኪ.ሜ ሲታደስ ከታቀደው 297 ኪ.ሜ የጥርጊያ መንገድ ውስጥ 400 ኪ.ሜ ተጠርጓል፣
- ከታቀደው የ44 ኪ.ሜ መንገድ ደረጃ ማሳደግ ውስጥ የ16.9 ኪ. ሜ ተሰርቷል፣

- 14 የእንጨት ድልድይ ታቅዶ ሁሉም ተሰርቷል፣
- ለመሥራት ከታቀደው 26 የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ 7 ት/ቤት ሲሰራ 19 እየተገነባ ነው፣
- 5 የሰው ጤና ኬላ ለመሥራት ታቅዶ 11 ተሰርቷል፣
- ለጤና አገልግሎት 3,412,189.30 ብር ሲወጣ 60 ፍሪጆች ተገዝቷል፣
- ከ1152 የባለሙያ ስልጠና ውስጥ 67ቱ ሰልጥነዋል፣

## 1.4 ደቡብ ክልል

- ከታቀደው 10,000 ቤተሰብ ሰፈራ ውስጥ 1,893 ሰፍረዋል፣

*መሠረተ ልማት*

- 18 የምድጃ ሞልድ ታቅዶ 19 ተሰራጭቷል፣
- ከታቀደው 10,000 ማገዶ ቆጣቢ ውስጥ 1,200 ተገዝቷል፣
- የ22 ት/ቤት ግንባታና የፊደል ገበታ፣ ጥቁር ሠሌዳ፣ ወንበር ተገዝቷል፣ /መጠኑ አልተጠቀሰም/
- ከታቀደው የ361 ኪ.ሜ ጥርጊያ መንገድ ውስጥ 177.1 ኪ/ሜ ተጠርጓል፣ እንዲሁም ከ297 ኪ.ሜ ጠጠር ማልበስ ውስጥ የ90.4 ኪ/ሜ ተከናውኗል፣
- ከታቀዱት 17 መጋዘኖች ግንባታ 17 ወፍጮ ቤት፣ 15 የጤና ኬላ፣ 16 የእንስሳት ጤና ኬላ፣ 18 የልማት ጣቢያ፣ ሠራተኞች መኖሪያ ቤት፣ 17 የልማት ጣቢያ ሠራተኞች ጽ/ቤት ውስጥ የተከናወነው 38% ብቻ ነው::

# ክፍል ሁለት፡- ከሠፈራ ውጭ የተከናወኑ የሌሎች የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ሥራዎች

## 2.1. ቤተሰብን መሠረት ያደረጉ ሥራዎች፣

### 2.1.1 ትግራይ ክልል

- ከ256,000 ቤተሰቦች ውስጥ 135,074ቱ በቤተሰብ ፓኬጅ እንዲሳተፉ ተደርጓል፣

**ሀ. ሰብል ልማት**

- ከታቀደው ከ3,405 ኩንታል ምርጥ የሰብል ዘርና 68 ኩንታል የአትክልትና ፍራፍሬ ምርጥ ዘር ውስጥ 4,272 ኩንታል ምርጥ የሰብል ዘርና 85 ኩንታል የአትክልት ምርጥ ዘር ተሰራጭቷል፣
- ከታቀደው 45,408 ሊትር ፈሳሽ 3,950 ኩንታል ዱቄት ፀረ-ተባይ መድኃኒትና 207 የመርጫ መሳሪያ ውስጥ 23,700 ሊትር ፈሳሽ 2,705 ኩንታል ዱቄትና 207 የመርጫ መሳሪያ ቀርቧል፣
- ከታቀደው የ160.83 ኩንታል የፍራፍሬ ዘር፣ 415,828 የፍራፍሬ ችግኞች፣ 2,691 የእጅ መሣሪያዎችና 4 የውኃ ፓምፕ ውስጥ 621.6 ኩንታል የፍራፍሬ ዘር፣ 50,395 የፍራፍሬ ችግኝ፣ 2,691 የእጅ መሣሪያዎች እና 4 የውኃ ፓምፕ ተገዝተዋል፣
- የታቀደው 4 መጋዘን ግንባታ በመካሄድ ላይ ነው፣

**ለ. እንስሳት ሀብት ልማት**

- ከታቀደው 500 የወተት ላሞች፣ 3000 በጐች፣ 30000 የዶሮ ጫጩቶች፣ 4000 እናት ዶሮዎች፣ 75000 የንብ ቀፎዎችና 1443 የተሻሻለ ማረሻ ግዢ ውስጥ 456 ላሞች፣ 1444 በጐች፣ 15000 ጫጩቶች፣ 2800 እናት ዶሮዎች፣ 62044 የንብ ቀፎዎችና 1443 ማረሻዎች በቤተሰብ ፓኬጅ ለታቀፉት ተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፣
- 112.5 ኩንታል የእንስሳት መኖ ዘር ለማቅረብ ታቅዶ 112.5 ኩንታል /100%/ ተገዝቶ ተሰራጭቷል፣
- የ4000 የባርካ ፍየሎችና የ1500 የደጋ በጐች ግዢ አልተከናወነም፣

- ለንብ እርባታ ማዕከሉ የ15000 የተለያዩ እቃዎችና የ90 ዘመናዊ ንብ ግዢ ተከናውኗል፣
- ከታቀደው የ2953 የዶሮ መመገቢያ ሳጥኖች፣ 29530 የዶሮ ጫጩቶችና 500 ኩንታል የዶሮ መኖ ውስጥ 2953 ሳጥኖች፣ 17360 ጫጩቶችና 2043.77 ኩንታል የዶሮ መኖ ተገዝቷል፣

### ሐ. መስኖ ልማት

- 100,000 የውኃ ኩሬዎች ለመቆፈር ታቅዶ 82,262 ተቆፍሯል፣
- ከታቀደው 3282900 ካ.ሜ የውኃ ማሰባሰቢያ ፕላስቲክ ውስጥ 448,000 ካ.ሜ ተገዝቷል፣
- 20,000 የጠብታ መስኖ ልማት መሳሪያ ታቅዶ 7,000 ሲገዛ እንዲሁም 200 በርሜሎች ግዢ ታቅዶ 200 ቀርቧል፣
- 1,025 አነስተኛ የውኃ መሳቢያ ፓምፕና 500 ትልልቅ የውኃ መሳቢያ ፓምፕ ታቅዶ የ1125 አነስተኛ ፓምፕ ግዢ ሲፈፀም የ500 ትላልቅ የውሃ መሳቢያ ፓምፕ ግዢ በሂደት ላይ ነው፣
- ለ513 የውኃ ቴክኒሻኖችና ለ128 ኤክስፐርቶች ስልጠና ተሰጥቷል፣

### መ/ ለሥራ አጥ ወጣቶች የሙያ ስልጠና መስጠት

- ለ452 ወጣቶች የሙያ ስልጠና ተሰጥቷል፣

## 2.1.2 አማራ ክልል

- ለ197,699 ቤተሰብ ተኮር ሥራ ተሰርቷል፣

### ሀ. የሰብል ልማት ፓኬጅና የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት

- ከታቀደው 8598 ቤተሰቦች ውስጥ 1,468 በብርዕና አገዳ ሰብል፣ 5,272 በጥራጥሬ ሰብል፣ 48 በቅመማ ቅመም ተሳትፈዋል፣ /በጠቅላላው 6,788 ነው/
- 4 ዲዝል ፓምፖች፣ 20 ወሸር ፓምፖችና 533,925 የስኬር ቁርጥራጭ ተገዝቷል፣ /ዕቅዱ አልተገለፀም/
- ከታቀደው 680.4 ቢቢም፣ 4,914 ገልባጭ ማረሻ፣ 17,500 ጠንካራ ክንድ፣ 80,200 ታይሬጀር፣ 52,100 ትሪድል ፓምፕ፣ 1,138 ዲዝል

ፓምፕ፣ 52,771 ድሪፕ ሲስተም እና 50,000 ስኩየር ሜትር የስርገት መከላከያ ጂኦሜምብሬን ውስጥ 89750 ቢቢም፣ 43,160 ታይሬጀር፣ 25,549 ትሪድል ፓምፕ ሲገዛ 50,000 ስኩየት ሜትር የስርገት መከላከያ ጂኦሜምብሬን ግዥ በሂደት ላይ ነው፡፡

## ለ. የእንስሳት ሀብት ልማት ፓኬጅ

- ከታቀደው 165,885 በጐች፣ 98,722 ፍየሎች፣ እና 407.84 ኩንታል የመኖ ዘር ውስጥ 89,764 በጐች፣ 66,607 ፍየሎችና 282.3 ኩንታል የመኖ ዘር ተገዝቷል፣
- 38083 በጐችና ፍየሎች እና 1106 የደልጋ ከብት ለመግዛት ታቅዶ 15858 በግና ፍየል እንዲሁም 1,475 ዳለጋ ከብት ተገዝቷል፣ /20,218 ቤተሰቦች ያሳተፈ ነው/
- ከታቀደው 48 ክልስ ክበድ ጊደሮችና 830 የአካባቢ ጊደሮች ውስጥ በቅደም ተከተል 10 እና 291 ተገዝቷል፣
- 19,579 የዶሮ ጫጩቶች ተገዝቷል፣ /የታቀደው 42,023 ነው/ /5247 ቤተሰቦችን ያሳተፈ ነው/
- 3,271 የሽግግር የንብ ቀፎ፣ 85,772 የቀፎ ርብራብና 2,827 የንብ መንጋ ተገዝቷል፣ /የታቀደው 21,042፣ 128,654 እና 7994 በቅደም ተከተል ነበር/
- 1516 የንግስት ንብ መለያ፣ 2058.33 ኪ.ግ ስም እና 24 ስም ማተሚያና ማር ማጣሪያ ቀርቧል፣ /የታቀደው 1,439፣ 5,136.33 እና ኪ.ግ ሰም እና 28 ስም ለማተሚያና ማር ማጣሪያ ነበር/
- 1,008.67 ኩንታል የመኖ ዘር ከታቀደው 1,331.84 ሲቀርብ 7,889 ኩንታል የእንሰሳት መኖ ዘር ተገዝቷል፣
- 9 ኩሬዎችን በማዘጋጀት የዓሳ እርባታ ዘዴን ለአርሶ አደር ለማስተዋወቅ ታቅዶ 2 የአሳ ኩሬዎች ተሰርተዋል፣

## ሐ. አነስተኛ መስኖ ልማት

- 10 ጥልቅ የውኃ ጉድጓድ ተቆፍሯል፣ 6 የግፊት መስኖ አውታርና 1 የስልት መስኖ አውታር ቀርቧል፣ /ዕቅዱ 18፣ 10 እና 1 ብቅደም ተከተል ነበር/
- 5 የውኃ ጉድጓድ ቁፋሮ ተከናውኗል፣ /ከ1996 የተላለፈ/

- 41 ወንዝ ጠለፋ፣ 890 ጉድጓድ ቁፋሮ፣ 72 ምንጭ ማጐልበትና፣ የውኃ ፓምፕ ግዢ ተፈጽሟል፣ /ዕቅዱ በቅደም ተከተል 54/ 2851፣ 292 እና 9 ነበር/

መ. ከግብርና ውጭ የገቢ ማስገኛ ሥራ

- በ14 የምግብ ዋስትና ወረዳዎች 1970 ወጣቶች ሰልጥነዋል፣ /ዕቅዱ 30 ወጣቶችን በቱሪስት ማስጐብኘት፣ 25 በዕደ ጥበብ እና 9 በምግብ ዝግጅት ሙያዎች እና በሌሎችም ነበር/

## 2.1.3 ኦሮሚያ ክልል

- 18918 ቤተሰብ በማሳተፍ የአንድ ቤተሰብ ገቢ 3500 ለማድረስ ቢታሰብም የፊዚካል ሥራ ዕቅዱን ለማወቅ አልተቻለም፣

ሀ. የተለያዩ የፍራፍሬ ዘሮች አቅርቦት

- ከታቀደው 41,000 የፍራፍሬ ችግኞች ውስጥ 41,000 ችግኞች በ1667 ቤተሰቦች ለምተዋል፣
- 322 ኪ.ግ የፍራፍሬ ዘሮች ተገዝቷል፣ /እቅዱ 1100 ኪ.ግ ነበር/
- 267 ኩንታል የትራትካሌ ስንዴ ተሰራጭቷል፣ /እቅድ 464 ኩንታል ነበር/

ለ. አነስተኛ መስኖ ልማት

- 3 አነስተኛ መስኖ ግንባታ እየተካሄደ ነው:: / እቅዱ 3 ነበር/
- የ4 አነስተኛ መስኖ ግንባታ ሲጠናቀቅ የ9ኙ በመካሄድ ላይ ነው /እቅዱ 13 ነበር/
- 7.5 ኪ.ሜ የመስኖ ቦዮች ተጠግነዋል:: /እቅዱ 9ኪ.ሜ ነበር/
- 9 የውኃ ሞተር ፖምፖች ተገዝተዋል:: /እቅዱ 13 ነበር/
- ከ20 ሄ/ር ማልማት የሚችል አነስተኛ መስኖ ልማትና 30 ሄ/ር ማልማት የሚችል ሌላ መስኖ ውስጥ 63% እና 99% በቅደም ተከተል ተከናውኗል:: /67 አርሶአደር ቤተሰቦችን ተጠቃሚ ለማድረግ የታቀደ/
- 300 ትሪድል ፖምፕና 357 ፋሚሊ ድሪፕ ተገዝቷል:: /እቅዱ በቅደም ተከተል 12,500 እና 627 ነበር/

- የ74 አዲስ ኩሬዎች ግንባታ እና የ5 የኩሬዎች ጥገና ተከናውኗል፡፡ /እቅዱ 114 እና 9 ነበር/

ሐ/ የብድርና ቁጠባ አገልግሎት

- ለ737 አባወራ አርሶ አደሮች 722,956 ብር ብድር ተሰጥቷል፡፡ /ዕቅዱ ለ240 አባወራ አርሶ አደሮች 2,285,277 ብር ነበር/

## 2.1.4 ደቡብ ክልል

ሀ. የሰብል ልማት

- የ12 የአዝርዕት ሠርቶ ማሳያ ጣቢያ፣ 2 የሰብል ዘርና 2 የአትክልትና ሥራሥር ማባዣ ጣቢያ ተከናወኗል፣፣ /ዕቅዱ 10,2,2 በቅደም ተከተል ነበር/

## 2.1.5 አፋር

ሀ. ሠብልና አትክልት ልማት ፓኬጅ

- 348 ኩ/ል የአዝርዕት ዘሮች እና 360 ኩ/ል ማዳበሪያ ተገዝቷል፡፡ /ዕቅዱ በቅደም ተከተል 1493.29 ኩ/ል እና 1230 ኩ/ል ነበር/
- 89 የእርሻ በሬዎች ተገዝተዋል፡፡ /ዕቅዱ 86 በሬዎች ለ43 ተጠቃሚዎች ነበር/

ለ. የእንሰሳት ሀብት ልማት ፓኬጅ

- 302 የሚደልቡ እንሰሳት፣ 46 ዘመናዊ የንብ ቀፎና 345 ዶሮዎች ተገዝቷል፡፡ /ዕቅዱ በቅደም ተከተል 700፣ 120 እና 420 ነበር/
- 710 ኪ.ግ የመኖ ዘር ለ152 ሄ/ር መሬት ተገዝቷል፡፡ /ዕቅዱ 710 ኪ.ግ ለ650 ሄ/ር ነበር/

ሐ. የእንሰሳት ጤና አጠባበቅ

- ለ786,000 እንሰሳት ህክምናና ለ566,000 እንሰሳት ክትባት ተሰጥቷል፡፡ /ዕቅድ ለ923,000 እና ለ1,800,000 ነበር/

**መ. መስኖ ልማት**

- *100 ሄ/ር መሬት በመስኖ ለምቷል፡፡ /ዕቅዱ 100 ሄክታር ለ200 ቤተሰብ ነው፡፡/*
- *200 ሄ/ር በመስኖ የግጦሽ መሬት ለማልማት ታቅዶ 200 ሄ/ር ለምቷል፡፡ /3 ባለአንድ ኪሎሜትር ቦዮች ሥራ ተከናወኗል/*
- *ለተጠለፈው የጉርፍ ውኃ 100 ኩንታል የበቆሎ ዘርና 20 የእርሻ በሬዎች ተገዝተዋል፡፡ /ዕቅዱ አልተገለፀም፡፡/*
- *115 ሄ/ር የእርሻ መሬት ተዘጋጅቷል፡፡ /ዕቅዱ 375 ሄ/ር ነበር/*
- *75 ሄ/ር መሬት ተመንጥሯል፡፡ /ዕቅዱ 100 ሄ/ር ነበር/*
- *በ200 ሄ/ር ላይ 200 ቤተሰቦች ዘር ዘርተዋል፡፡ /ዕቅዱ አልተገለፀም/*
- *45 ሴት አርብቶ አደሮች በሙያ ሰልጥነዋል፡፡ /ዕቅዱ አልተገለፀም/*
- *96 የወረዳና የቀበሌ ግብረ ኃይል የልምድ ልውውጥ አድርገዋል፡፡ /ዕቅዱ አልተገለፀም/*

## 2.1.6 ሶማሌ ክልል

- *ለክልሉ ከተመደበው በጀት 3/4 ለመለስተኛ የግድብ ሥራና ለገጠር መጠጥ ውሃ የዋለ ሲሆን፣ ሥራው በመካሄድ ላይ ነው፡፡ በቀሪው 1/4 በጀት የተከናወኑ ሥራዎች፡-*

**ሀ. የተሻሻሉ የበግና ፍየል ዝርያዎች አቅርቦት**

- *615 በጉች፣ 700 ፍየሎች፣ 22 በሬዎች፣ 70 የንብ ቀፎ፣ ተገዝቷል፡፡ /ዕቅዱ 450 450 450 እና 70 ነበር/*

**ለ. የዘር አቅርቦት**

- *በታቀደው መሠረት 2700 ኩንታል የእህል ዘር፣ 350 ኪ.ግ የአትክልት ዘር፣ 275 ሺ. የድንች ዘር፣ 1200 ኩንታል ማዳበሪያ እና 5600 የእርሻ መሳሪያ ግዢ ተከናውኗል፡፡*
- *በታቀደው መሠረት 700 ኩንታል የእህል ዘር፣ 275 ኪ.ግ የአትክል ዘር፣ 100 ኩንታል የድንች ዘር፣ 150 ኩንታል ሰሊጥ፣ 82500 የስኳር ድንች*

*ቁርጥራጭ፣ 250 ኩንታል ማዳበሪያ እና 4250 የእርሻ መሳሪያ ግዢ ተፈጽሟል::*

*ሐ. መስኖ ልማት*

- *6 ታቅዶ 2 አነስተኛ መስኖ ፕሮጀክቶች ተጠናቀዋል:: /95 ሄክታር በማልማት 948 አባወራ አርዶአደሮችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው/*
- *120 ኩሬዎች ተቆፍረዋል:: /ዕቅዱ 430 ነበር/*
- *ለ201 ኩሬዎች ግንባታ የማቴሪያል ግዢ ተከናወኗል:: /ዕቅዱ አልተጠቀሰም/*

*መ. አፋር አካባቢ ለሰፈሩ ሠፋሪዎች መኖሪያ ቤት መስራት*

- *የ100 ቤቶች ግንባታ፣ የእርሻ መሣሪያዎች ግዢና 100 ሄክታር የእርሻ መሬት ተዘጋጅቷል:: /ዕቅዱ አልተጠቀሰም/*

*ሠ. በእርሻ ልማት ለሚሳተፉ ሴቶች የጓሮ አትክልት ዘር ማቅረብ*

- *690 ኪ.ግ የአትክልት ዘርና 2400 የተለያዩ የእርሻ መሣሪያዎች ተገዝተዋል:: /ዕቅዱ 1190 ኪ.ግ እና 3900 ነበር/ እነዚህ የተገዙት ዘርና መሣሪያዎች ለ1300 የገጠር ሴቶች ተከፋፍለዋል::*

## 2.1.7 ድሬዳዋ

*ሀ. ግብርና ልማት*

- *130 ኪ.ግ የአትክልት ዘር ተገዝቷል:: /ዕቅዱ 299 ኪ/ግ ነበር/*
- *2500 የዋንኬ በጐች ለማድለብ ተገዝተዋል:: / ዕቅዱ አልተገለፀም/*
- *2 የአገር ወስጥ የወተት ላሞች ተገዝተዋል:: /ዕቅዱ 60 ነበር/*
- *31 የወተት ግመሎች ተገዝተዋል:: /ዕቅዱ 20 ነበር/*
- *470 ዶሮዎች ተገዝተዋል:: /ዕቅዱ 7000 ነበር/*
- *250 የንብ ቀፎዎች ተገዝተዋል:: /ዕቅዱ 2000 ነበር/*
- *ብር 1,100,000 ብድር ተመድቦ 2000 ሴቶች በአነስተኛ ንግድ፣ በእንሰሳት ማድለብና በጓሮ አትክልት 334 ወንዶችና 391 ሴቶች በድምሩ 725 ቤተሰቦች ተጠቃሚ ሆነዋል::*

***ለ. መስኖ ልማት***

- ***ከታቀዱት 6 አነስተኛ መስኖዎች ውስጥ 2 ተጠናቀዋል:: /95 ሄክታር በማልማት 948 አባወራዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ/***
- ***120 ኩሬዎች ተቆፍረዋል:: /ዕቅድ 430 ነበር/ እንዲሁም 109 እየተቆፈረ ነው::***
- ***ለ201 ኩሬዎች ግንባታ የዕቃ ግዢ ተፈጽሟል:: /የተገዛው ዕቃ መጠኑ አልተገለፀም/***

### ***2.1.8 ሐረሪ ክልል***

***ሀ. የተቀናጀ የኤክስቴንሽን ፓኬጅ***

- ***385 አባወራዎች በኤክስቴንሽን ተሳትፈዋል:: /ዕቅዱ 500 ነበር/***
- ***500 ኩንታል ማዳበሪያ፣ 25 ኩንታል ምርጥ ዘር፣ 20 ኩንታል የአትክልት ዘርና 1.5 ኩንታል ፀረ-ተባይ መድኃኒት ተገዝቷል:: /ዕቅዱ አልተጠቀሰም/***
- ***50 አርሶ አደር አባወራዎች በእንስሳት ሀብት ፓኬጅ ተሳትፈዋል:: /ዕቅዱ 100 ነበር/***
- ***300 የተሻሻለ የዶሮ ዝርያዎች፣ 279 የርቢ ፍየል፣ 39 የወተት ላምና 30 ቀፎ ተከፋፍሏል:: /ዕቅዱ አልተጠቀሰም/***

***ለ. የውኃ ማቆር***

- ***1000 ኩሬዎች ተቆፍረዋል:: /ዕቅዱ 250 ነበር/***

## ***2.2 ማህበረሰብ ተኮር የልማት ሥራዎች***

### ***2.2.1 ትግራይ ክልል***

***ሀ. ግብርናና ተፈጥሮ ሀብት ልማት***

- በ414.5 ሄክታር የተፋሰስ ቦታዎች ላይ ችግኝ ተተክሏል፡፡ /ዕቅዱ 21550 ሄክታር ነበር/ በእነዚሁ ተፍሰስ ቦታዎች 455 ኩንታል የሣር ዘር ተተክሏል፡፡

**ለ. በገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከላት የግብርና አሠራር ሠርቶ ማሣያዎች ማካሄድ**

- በ494 ሄ/ር ላይ የአስተራረስና የዘር አዘራር ሰርቶ ማሳያ፣ 408.3 ኩ/ል ምርጥ ዘር፣ 1041 ኩ/ል ማዳበሪያ አቅርቦትና በ263 ሄ/ር መሬት ላይ የአረም ቁጥጥር ሥራ ተሰርቷል፡፡ /ዕቅዱ በቅደም ተከተል 593 ሄ/ር፣ 408.3፣ 1041 እና 263 ነበር/

**ሐ. የገጠር መጠጥ ውኃ**

- በዕቅዱ መሠረት የ7 ጥልቅ ውኃ ጉድጓድ፣ የ77 መለስተኛ የውኃ ጉድጓዶችና፣ የ4 የውኃ ጉድጓድ ጥናት ተከናውኗል፡፡
- በዕቅዱ መሠረት የ4 ከጣሪያ ላይ የሚፈስ ውኃ ማሰባሰብ ሥራና የ7 አነስተኛ የውኃ ጉድጓድ ዲዛይን ሥራ ተሰርቷል፡፡
- 15 ጥልቅ የውኃ ጉድጓድ ተቆፍሯል፡፡ /ዕቅዱ 16 ነበር/
- የ1 ሪግ (Rig) ግዢ እየተከናወነ ነው፡፡
- ከታቀዱት 77 ጉድጓዶች ውስጥ 59 ጉድጓዶች ተቆፍሯል፡፡ በእነዚህ ጉድጓዶች 22000 ቤተሰብ ተጠቃሚ ሆኗል፡፡

**መ. ገጠር መንገድ**

- 90.2 ኪ/ሜ መሬት ተመንጥሯል፣ 68.5 ኪ/ሜ መሬት ተስተካክሏል፣ 28.6 ኪ/ሜ አፈር ተጠቅጥቋል፣ 8 መካከለኛ ድልድይና 5 ትላልቅ ድልድዮች ተሰርተዋል፣፣ /ዕቅዱ በቅደም ተከተል 68.2 ኪ/ሜ፣77 ኪ/ሜ፣ 20 እና 8 ነበር/

**ሠ. ህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ**

- በዕቅዱ መሠረት የ22 መጋዘኖችና /3000 ኩንታል የሚይዙ/ እና የ1 መጋዘን /300 ኩንታል የሚይዝ/ ግንባታ ተከናውኗል፡፡

ረ. አቅም ግንባታ

- 1982 ባለሙያዎች ሰልጥነዋል:: /ዕቅዱ አልተጠቀሰም/
- 124 አመራር አካላትና 36 ሠራተኞች ሰልጥነዋል:: /ዕቅዱ በቅደም ተከተል 144 እና 36 ነበር/
- 30 ሂሣብ ሠራተኞችና 68 የገበያና ብድር ኤክስፐርቶችና ኦዲተሮች ሰልጥነዋል:: /ዕቅዱ 30 እና 68 ነበር/
- በዕቅዱ መሠረት ለ150 ባለሙያዎች ለምግብ ዋስትና ዕቅድ ላይ ግንዛቤ ጨብጠዋል::
- 74 ባለሙያዎችና 1186 ፎርማኖች /የኩሬ ቁፋሮ/ ሰልጥነዋል:: /እቅዱ አልተገለፀም/
- የ9 ዩኒየኖች መሥራች አውደ ጥናት ተካሂዷል:: /ዕቅዱ ለ10 ነበር/
- 176 ሰዎች የግምገማ አውደ ጥናት ተካትተዋል:: /ዕቅድ አልተገለፀም/
- በተመረጡ 6 ወረዳዎች የምግብ ዋስትና ፕሮግራም አፈፃፀም ያስገኘውን ውጤት ለመገምገም የሚረዳ ጥናት በብር 38,500 በመካሄድ ላይ ነው::

## 2.2.2 አማራ ክልል

ሀ. ገጠር መንገድ

- 36.92 ኪ/ሜ መንገድ ሲሰራ 3.04 ኪ.ሜ እየተሰራ ነው፣ 2 ድልድይ ተሰርቷል፣ 10 ዶዘር ተጠግኗል፣ /ዕቅዱ 39.96 ኪ/ሜ አዲስ መንገድ፣ 5 የወንዝ ድልድይ ግንባታና 10 ዶዘር ጥገና ነበር/
- 432 ኪ.ሜ አዲስ መንገድ ተሰርቷል፣ 317.8 ኪ/ሜ መንገድ ተጠግኗል፣ 1 ድልድይ ግንባታና 125 ፎርዶች ተሰርቷል:: /ዕቅዱ 754.64 ኪ.ሜ፣ 397.185 ኪ.ሜ፣ 2 ድልድይና 168 ፎርድ ነበር/

ለ. የገጠር መጠጥ ውኃ

- 210 ምንጮች፣ 157 የውኃ ጉድጓድና 13 የውኃ ጉድጓድ ጥገና ተሰርቷል:: /ዕቅዱ 286,625 እና 23 ነበር/ ይህም 35,817 ቤተሰቦችን ተጠቃሚ አድርጉአል::

### ሐ. የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል ግንባታ

- 337 ማዕከላት ተገንብተዋል፡፡ /ዕቅዱ 330 ነበር/

### መ. መጋዘን ግንባታ

- 10 መጋዘኖች ተሰርተዋል፡፡ /ዕቅዱ 13 ነበር/

### ሠ. ተፈጥሮ ሀብትና ተፋሰስ ልማት

- 187 ኩንታል የተለያዩ ዘሮች፣ 96.4 ኩንታል ፖሊቲን ቲዩብና 774 ሜ ኪዩቢክ ጋቢዮን ቀርቧል፡፡ /ዕቅዱ 241፣ 46.6 እና 708.3 ነበር/
- 22,759,000 የዛፍ ችግኝ ፈልቷል (እቅዱ 21,029,000 ነበር)
- 2329 ሄ/ር የእርከን ሥራ፣ 282,449 ኪዩቢክ የክትር ሥራ፣ 282,912 ትሬንች፣ 23,058 ሚ.ኪዮብ የጉርፍ መቀልበሻ ሥራ፣ 541,801 ማይክሮቢዝንና 313,809 አይብሮቤተርን ተሰርጓል (እቅዱ አልተገለፀም)

### ረ. ማገዶ ቆጣቢ ቴክኖሎጂን ማስተዋወቅና ማስፋፋት

- በእቅዱ መሠረት 1447 የፈጠነች ምርጥ ምድጃና 43,410 የምድጃ ማምረቻ ጣውላ ተገዝቷል፡፡

### ሰ. አቅም ግንባታ

- 110 ባለሙያዎች፣ 406 የልማት ጣቢያ ሠራተኞችና 1908 አርሶ አደሮች ሰልጥነዋል፡፡ /ዕቅዱ አልተጠቀሰም/
- 76 የህብረት ሥራ አመራር አካላትና 135 አመራርና ባለሙያዎች ሰልጥነዋል፡፡ እንዲሁም 35 አመራር አባላት የልምድ ልውውጥ አርገዋል፡፡ /እቅዱ አልተጠቀሰም/
- 208 የወረዳ አስፈጻሚ አካላት አውደ ጥናት ተሳትፈዋል (እቅዱ አልተገለፀም)
- 103 የውኃ ኮሚቴ አባላት ሰልጥነዋል (እቅዱ አልተገለፀም)

### 2.2.3 ኦሮሚያ ክልል

**ሀ. የቡና ልማት**

- 5 የቡና ችግኝ ጣቢያና 1 የቡና ዘር ማባዣ ተቋቁሟል:: /እቅዱ 6 እና 1 ነበር/
- በእቅዱ መሠረት 24000 የቡና ችናኞችና 9830 ጉድጓዶች ተዘጋጅተዋል::
- 91.9 ኩ/ል የቢጫ ቡና ዘር ተገዝቶ ተዘርቷል /እቅዱ 100 ኩ/ል ነበር/

**ለ. ደን ልማት**

- 22 የደን ችግኝ ማፊያ ጣቢያ ተቋቁሟል /እቅዱ 35 ነበር/

**ሐ. የገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከልና የእህል ማጋዘን ግንባታ**

- 86 ማሰልጠኛ ማዕከላት ተገንብቷል:: /እቅዱ 136 ነበር/
- ካለፈው ዓማት የተረፈው 4 ማዕከል ተገንብቷል::
- በእቅዱ መሠረት 11 የእህል ማጋዘኖች ተሰርተዋል::

**መ. የእንስሳት እርባታና ጤና አጠባበቅ**

- 1 የወተት ማቀነባበሪያ ጣቢያና 11 የእንስሳት ጤና ኬላ ግንባታ ተከናውኗል:: /እቅዱ 1 እና 20 ነበር/

**ሠ. የገጠር ኢነርጂ ማስፋፋት**

- 321 ዘመናዊ ምድጃ ተገዝቷል / እቅዱ 461 ነበር/

**ረ. የገጠር ንፁህ የመጠጥ ውኃ አገልግሎት**

- 5 ምንጮች ጐልብተዋል / እቅዱ 41 ነበር
- የታቀደው 3 ምንጭ ጥገና እና 6 የእንስሳት ውኃ መጠጫ ገንዳ አልተሰራም
- 3 የውኃ ጉድጓድ ተጠናቋል / እቅዱ 15 ነበር/

ሰ. ገጠር መንገድ

- 18.19 ኪ.ሜ አዳስ መንገድ ተሰርቷል / እቅዱ 21 ኪ.ሜ.ነበር/
- 80 ሜ.ርዝመት ያለው ድልድይ ተሰርቷል። /ከዕቅድ ውጪ/
- 89.5 ኪ.ሜ መንገድ ተጠግኗል /ዕቅዱ 201 ኪ.ሜ.ነበር/

ሸ. አርብቶ አደር ልማት

- በዕቅዱ መሠረት 6 የወተት ማቀነባበሪያና መሸጫ ማዕከላት ተገንብተዋል።
- 12 ኩሬዎች ታድሰዋል። እንዲሁም 2 ከቤት ጣሪያ ላይ ውኃ ማሰባሰቢያ ተሰርቷል። /እቅዱ 16 እና 4 ነበር/

ቀ. አቅም ግንባታ

- 7596 ባለሙያዎች ሰልጥነዋል / እቅዱ 4242 ነበር/
- 14 ቴክኒሺያኖች ሰልጥነዋል / እቅዱ 117 ነበር/
- 13768 አርሶ አደሮች ኮንፈረንስ ተካፍለዋል /ዕቅዱ 15298 ነበር/

## 2.2.4. ደቡብ ክልል

ሀ. የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ

- 8939 ኪ.ግ የዛፍ ዘር ሲገዛ፣ 110 ሚሊዮን የዛፍ ችግኝ ተዘጋጅቷል። እንዲሁም 14891 ሄ/ር የተፈጥሮ ደን ተከልሏል። /እቅዱ በቅደም ተከተል 710 ኪ.ግ፣ 53.23 ሚሊዮን እና 10,600 ሄ/ር ነበር/
- 7060 ኪ/ሜ እርከን፣ 1217 ኪ.ሜ ክትር ሥራ ፣ 413136 ትሬንች ቁፋሮ፣ 479061 የማይክሮቤዚን ቁፋሮ እና 49163 ሜ/ኩብ ኮምፖስት ተዘጋጅቷል። / እቅዱ በቅደም ተከተል 23492፣ 843፣685,250፣1,041,000 እና 20,080 ነበር/

ለ. በግብርና ሙያ ለባለሙያዎች ስልጠና መስጠት

- 35 የወረዳ ባለሙያዎችና 194 የልማት ሰራተኞች በአትክልትና ፍራፍሬ ሰልጥነዋል። እንዲሁም 158 ባለሙያዎችና 155 ሰራተኞች በሰብል ልማትና ጥበቃ ሰልጥነዋል። /ዕቅዱ 30 እና 256 በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ሲሆን 132 እና 400 በሰብል ልማት ነበር/

- 147 ለቅመማ ቅመም፣ 56 በሐር ልማት፣ 47 በወተት ከብት አያያዝ፣ 287 በገጠር ሴቶች እና 3551 በተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ሰልጥነዋል:: /ዕቅዱ በቅደም ተከተል 60፣90፣45፣312 እና 630 ነበር/

### ሐ. የገጠር የመጠጥ ውኃ አቅርቦት

- 43 ጉድጓድ ተቆፍሯል፣ 5 ምንጮች ተገንብተዋል:: 3 ምንጮች የማከፋፈያ ሥራና የ2 ጉድጓድ ቁፋሮ ተጠናቋል:: / ዕቅዱ 44፣5፣ እና 3 ነበር/
- 201 የእጅ ፓምፖች፣ 58 ፓምፖች ሲጠገኑ 18 ጉድጓዶች ተጠርገዋል / ዕቅዱ በቅደም ተከተል 280፣20 እና 20 ነበር/
- በእቅዱ መሠረት 200 ኤፍሬዲብ ፓምፕ፣ 80 ኢንዲያን ማርክ እና 25 የእጅ ፓምፕ ጥገና መሳሪያና 29 ኮንክሪት ሞልድና ቼይን ብሎክ ግዢ ተከናውኗል::
- 10 የውኃ ተቋማት ጠጋኞች፣ 21 የውኃ ኮሚቴ አባላትና 5 የውኃ ተንከባካቢዎች ሰልጥነዋል:: /እቅዱ 10፣ 60 እና 30 ነበር/

### መ. የአርብቶ አደር ልማት

- 23 የውኃ ገንዳ፣ 5 የውኃ ጉድጓድና 6 ኩሬ ተቆፍሯል:: /እቅዱ 67፣11 እና 6 ነበር/
- 10 የውኃ መሳቢያ ጄኔሬተርና 6 በነፋስ የሚሠራ ፓምኘ ተገዝቷል:: /እቅዱ 3 እና 160 ነበር፣
- በእቅዱ መሠረት 1 የእንስሳት ክሊኒክ እና 13 የእንስሳት ጤና ኬላ ተገንብቷል::
- 30 የአንስሳት ጤና ተቆጣጣሪዎች ሰልጥነዋል:: /እቅዱ 35 ነበር/
- 13 የመኖ ሠርቶ ማሣያ ሲቋቋም 110 የተፈጥሮ ግጦሽ ተሻሽሏል:: /እቅዱ 12 እና 300 ነበር/
- 150 የንብ ቀፎ ሲቀርብ 9 የእንስሳት ገበያ ማዕከላት ተቋቁሟል:: /እቅዱ 180 እና 10 ነበር/

### ሠ. የሰብል ልማት

- 12 የአዝርዕት ሠርቶ ማሳያ፣ 2 የሰብል ዘርና 2 የአትክልትና ሥራ ሥር ማብዣ ጣቢያ ተቋቁሟል:: /እቅዱ በቅደም ተከተል 10፣ 2 እና 2 ነበር/

### 2.2.5 አፋር ክልል

#### ሀ. ሰብል ልማትና ጥበቃ

- በ15 ወረዳዎች የተባይ አሰሳ ተደርጓል።/እቅዱ 18 ነበር/
- 361 ሄ/ር መሬት ከፕሮሶፒስ አረም እና 18 ሄ/ር መሬት ከፓርቲኒየም አረም የመከላከል ሥራ ተሠርቷል። /እቅዱ በቅደም ተከተል 500 እና 8750 ሄ/ር ነበር/
- 13400 ሊትር ፈሳሽ፣ 6588 ኪ.ግ ዱቄት ፀረ-ተባይ መድኃኒትና 20 ሳይፋን ፓምፖች ግዢ ጨረታ ወጥቷል። / ዕቅዱ 17,616 ሊትር፣ 2,475 ኪ.ግ እና 20 ነበር/

#### ለ. ተፈጥሮ ሀብት ልማት

- 4.744 ኪ.ሜ የአፈር እርከን እና 36 ሜ.ኩብ ክትር ተሰርቷል። /እቅዱ 4.5 ኪ.ሜ እና 36 ሜ. ኩብ ነበር/
- 14,4000 ችግኝ የፈላ ሲሆን፣ 5 የችግኝ ማፍያ ጣቢያ ተቋቁሟል። /እቅዱ 135,000 እና 12 ነበር/
- በእቅዱ መሠረት 2 የችግኝ ማፍያ ጣቢያዎችን መልሶ የማቋቋም ሥራ ተከናውኗል።

#### ሐ. መጠጥ ውኃ

- ከጠቅላላው 28 የመጠጥ ውኃ ግንባታ እቅድ ውስጥ 7 የመጠጥ ውሃ ጉድጓድ መልሶ የማቋቋም ሥራ፣ 4 የውኃ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራና 13 የውኃ የማከፋፈያ ግንባታ ተከናውኗል።
- የታቀደው የ16 የመጠጥ ውኃ ግንባታ በዕቅዱ መሠረት እየተሠራ ነው
- በዕቅዱ መሠረት 20 የውኃ መሳቢያ ፓምፖች ከአማራ ክልል ተገዝተዋል።
- 55 ፓምፖች ከትግራይ ክልል ተገዝተዋል። /በዕቅድ አልተያዘም/
- 75 የውኃ መሳቢያ ሞተር ግዢ እና 125 ተጨማሪ ፓምፖች እንዲገዛ ተወስኗል። /ዕቅዱ አልተገለፀም/
- 29329 ሜ.ኩብ አፈር የተሰበረ የወንዝ ዳርቻ መዝጋት፣ 10 ኪ.ሜ የወንዝ አመራርና 16 ኪ.ሜ የጐርፍ መከላከያ ሥራ ተሰርቷል። /ዕቅዱ አልተገለፀም/

- በዕቅዱ መሠረት 15 ኪ.ሜ የወንዝ ዳር ምንጣሮና 7500 ሜ. የተሰበሩ የወንዝ ጠርዞች ተጠግኗል፡፡
- በዕቅዱ መሠረት 20 ኪ.ሜ የውኃ ቦይና ካናል ጠረጋና የ2 ኪ.ሜ ደለል ጠረጋ ተሰርቷል፡፡
- 4 ወንዝ ጠለፋ ሥራ ተሰርቷል፡፡ /ዕቅዱ 6 ነበር/
- 3 ኩሬ በማሽንና 2 ኩሬ በህብረተሰቡ ተሳትፎ ተሰርቷል፡፡ /ዕቅዱን አይገልፅም/
- 9 ኩሬዎች ከታቀደው 10 ውስጥ በ3 ወረዳዎች ተቆፍሯል፡፡
- 4.5 ኪ.ሜ የውኃ ቧንቧ መዘርጋት ተከናውኗል፡፡ /ዕቅድ አልተገለፀም/
- የ2 ፓምፕና 2 ጀኔሬተር ተከላ ሥራ ተጠናቆ የ1500 ሜትር ርዝመት ቧንቧ የመዘርጋት ሥራ ተከናወኗል፡፡ /ዕቅድ አልተገለፀም/

*መ. ገጠር መንገድ*

- 53.03 ኪ.ሜ መንገድ ተሰርቷል፡፡ /ዕቅዱ 89 ኪ.ሜ ነበር/

*ሠ. ህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ*

- አንድ 1500 ኩንታል የመያዝ አቅም ያለው መጋዘን በመገንባት ላይ ነው፡፡ /ዕቅዱ አልተገለፀም/
- 225000 ብር ለጨው ግብይት ሥራና 375000 ብር ለእንስሳት ማድለብ ሥራ ተሰጥቷል፡፡ /ዕቅድ አልተገለፀም/

*ረ. ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ክትትል*

- 110 የክልልና የወረዳ ፈፃሚና አስፈጻሚ አካላት ዓውደ ጥናት ተካሂዷል፡፡ /ዕቅዱ አልተገለፀም/
- 63 ባለሙያዎች ሰልጥነዋል፡፡ /ዕቅዱ አልተገለፀም/
- 45 ሴት አርብቶ አደሮች ሰልጥነዋል /ዕቅዱ አልተገለፀም/
- 96 ግብረ ኃይል አባላት የልምድ ልውውጥ አድርገዋል፡፡ /ዕቅዱ አልተገለፀም/

### ሰ. ሥልጠና

- ከታቀደው 178 ውስጥ 95 ሰዎች ሰልጥነዋል፡፡ /በስጋ ምርት ማሻሻያ ፓኬጅ/
- በማር ምርት ከዕቅዱ 137 ሰዎች ውስጥ 9ኙ ሰልጥነዋል፡፡
- በዕቅዱ መሠረት 7 ባለሙያዎች በንብ እርባታ ሰልጥነዋል፡፡
- 17 ሀኪሞችና ረዳት ሀኪሞች ሰልጥነዋል፡፡ /ዕቅዱ 25 ነበር/
- 25 የእንሰሳት ጤና ቴክኒሺያኖችና ሥጋ መርማሪዎች ሰልጥነዋል፡፡ /ዕቅዱ 30 ነበር/
- በዕቅዱ መሠረት 4 ባለሙያዎች በእንሰሳት ተዋፅኦ፣ ቆዳና ሌጦ ሰልጥነዋል፡፡

## 2.2.3 ሶማሌ ክልል

### ሀ. መስኖ ልማት

- ወደ መስኖ ቦታ የሚወስድ መንገድ 26700 ሜትር የመሬት ጠረጋና 34000 ካ.ሜ የውኃ መንጠፍጠፍ ሥራ ተሰርቷል፡፡ /ዕቅዱ አልተገለፀም/
- 400 ሄ/ር መሬት ለመስኖ ተዘጋጅቷል፡፡ /ዕቅዱ 1000 ሄ/ር ነበር/
- ከታቀደው 20 ሄ/ር መሬት ለማልማት የሚችል የመስኖ ውሃ ቦይና የውሃ መቀልበሻ ሣጥን ውስጥ 70% ተከናወኗል፡፡
- 1 የውኃ መሳቢያ ፓምፕ ማስቀመጫ ግንባታ በዕቅዱ መሠረት ተሰርቷል፡፡

### ለ. የሰውና የእንስሳት ጤና ኬላዎችና ቢርካዎች ግንባታ

- 1 የእንስሳት ጤና ኬላና 2 የሰው ጤና ኬላ በዕቅዱ መሠረት ተገንብቷል፡፡
- ለ3 ቢርካ አጥርና ጣሪያ በዕቅዱ መሠረት ተሰርቷል፣
- በተለያዩ ወረዳዎች 3፣ 2 እና 2 በድምሩ 7 የውኃ ቢርካዎች በዕቅዱ መሠረት ተገንብተዋል፡፡

### ሐ. ገጠር መንገድ

- 9.6 ኪ.ሜ መንገድ በግሬደር ተስተካክሏል፡፡ /ዕቅዱ 10 ኪ.ሜ ነበር/
- 4 ድልድዮች ተገንብተዋል፡፡ /ዕቅዱ 6 ነበር/

- ከዕቅድ 17.5 ኪ.ሜ ውስጥ ሁሉም መንገድ ተጠርጓል፡፡ እንዲሁም በዕቅዱ መሠረት 17.5 ኪ.ሜ መንገድ ተሰትካክሏል፡፡

መ. የመጠጥ ውኃ

- 11 ጥልቅ የውኃ ጉድጓድ ተቆፍሯል፡፡ /ዕቅድ 35 ነበር/
- ከዕቅዱ ውጭ 2 ጄኔሬተር ተገዝቷል፡፡
- በዕቅዱ መሠረት 2 ሰብመርሰብል (Submersible) ፓምፖችና 2 ጄኔሬተሮች ተገዝተዋል፡፡
- የውኃ መሳቢያ ሞተር ግዢ እየተካሄደ ነው፡፡ /በዕቅድ ተይዞ ነበር/
- ከውሃ ልማት ጋር በተያያዘ 104 አርቴኾኖች ሰልጥነዋል፡፡ /በዕቅድ አልተያዘም/
- ለ20 ወረዳዎች በብር 12.0 ሚለዮን የውሃ መሳቢያ ሞተር ግዥ በሂደት ላይ ነው፡፡

ሠ. የእንሰሳት ጤና ጥበቃ

- በ1.733 ሚሊዮን ብር መድኃኒት፣ ክትባትና፣ የህክምና ዕቃ ተገዝቷል፡፡ /ዕቅዱ 2.32 ሚሊዮን ሲሆን፣ መጠኑን አይገልፅም/
- በ225,000 ብር የእንሰሳት ህክምና ተሰጥቷል፡፡ /ዕቅዱና መጠኑ አልተገለፀም/
- በ23775 ብር የላብራቶሪ ኬሚካልና ዕቃዎች ተገዝቷል፡፡ /በዕቅዱ አልተጠቀሰም/ እንዲሁም የተገዛውን ቁጥር አያሳይም/

ረ. ሥልጠና

- በዕቅድ መሠረት 50 የልማት ጣቢያ ሠራተኞችና 55 የክልልና የወረዳ ባለሙያዎች ሰልጥነዋል፡፡
- በዕቅዱ መሠረት ለ30 ሴቶችና ለ1300 የገጠር ሴቶች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

## 2.2.7 ድሬዳዋ

ሀ. የመጠጥ ውኃ

- 2 ጉድጓድ ተቆፍሯል፡፡ /የታቀደው 8 ነበር/

- በዕቅድ መሠረት የ3 መጠጥ ውኃ ፕሮጀክቶች አጠቃላይ ሥራ ተከናውኗል፣

**ለ. አፈርና ውኃ ጥበቃ**

- 138 ኪ.ሜ የድንጋይ እርከን፣ 6 ኪ.ሜ የማሳ ላይ እርከን፣ 22,000 ሜ/ኩብ፣ የድንጋይ ክትር፣ 3,365 ሜ/ኩብ የጐርፍ ውኃ ማቆሪያና 7,173 ሜ/ኩብ የጐርፍ መቀልበሻ ተሰርቷል፡፡ /ዕቅዱ በቅደም ተከተል 180፣ 60፣ 13,000፣ 4,200 እና 12,000 ነበር/
- 25 ሄ/ር መሬት ዝግጅት፣ 11.5 ኪ.ሜ የገጠር መንገድ፣ 2,776 የችግኝ መትከያ ቁፋሮና 1,000 ሜ/ኩብ ፍግ ወደ እርሻ ተጉዟል፡፡ /ዕቅዱ በቅደም ተከተል 80፣ 7፣ 25,000 እና 178 ሜ.ኩብ ነበር/

**ሐ. መንገድ ሥራ**

- የ7 ኪ.ሜ መንገድ ሥራ በብር 500,000 ለማካሄድ ታቅዶ በማሽነሪ እጥረት ምክንያት አልተከናወነም፡፡